DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ኅዳር (November) 10, 2014

ውድ ቤተሰቦች፤

በዚህ በፀደይ ወራት፣ DC-CAS ለኮሌጅ እና ለሙያዎች የዝግጁነት ብቁነትን ትምህርትን በሚገመግም ቡድን ቅንጅት (Partnership for Assessment of Readiness for College and Careers) አማካይነት በተዘጋጀ PARCC በሚባል አዲስ ፈተና ይተካል። ይህ ፈተና፣ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ከሚማሩት ትምህርት ጋር ይዛመዳል። የተማሪዎች የትምህርት ውጤት እርከንን ከፍ (to raise the bar) በማድረግ፣ ተማሪዎች ሁሉ ለኮሌጅ፣ ለሙያ እና ለሕይወት ስኬታማነት በጥርጊያ ጎዳና ላይ እንዲጓዝ ለማድረግ በ 2011 ከመሠረትነው (adopted) ከስቴቱ የጋራ ዋና መስፈርት ጋር (Common Core State Standards) ይጣጣማል።

አዲሱ የ PARCC ፈተና፣ ተማሪዎች በንባብ፣ በጽሑፍ እና በሂሳብ ምን እንደሚያወቁ ለማሳየት የተሻለ እድል ይሰጣቸዋል። ፈተናው በተጨማሪ የልጅዎን በጥብቅ የማሰብን፣ ችግሮችን በጥበብ የመፈታተን እና በግልጽ ሀሳብ የመለዋወጥን ችሎታ በተሻለ መንገድ ለመመዘን ያስችላል። የ PARCC ፈተና በሙሉ በኮምፒዩተር ይወሰዳል። ጥያቄዎቹም፣ የጽሑፍ እና በኮም ፒዩተር የምልልስ መልሶችን፣ (interactive responses)፣ በግራፍ ላይ መስመር ማስመርን፣ ወይንም ከታሪክ ድርጊቶችን በትክክለኛው ቅደም ተከተል ማስቀመጥን ይጠይቃሉ።.

ይህ፣ ተማሪዎች እስከ ዛሬ ሲወስዱ ከነበሩት፣ ከለመዱት ፈተና ትልቅ ለውጥ ይኖረዋል። ተማሪዎች በፈተናው የሚቻላቸውን ያህል እንዲሠሩ ለመርዳት በሚገባ ተዘጋጅተናል። ይህ አዲስ፣ ይበልጥ ተፈታታኝ ፈተና ልጅዎ በከፍተኛ ደረጃ ውጤት እን ዲያመጣ ለመርዳት እጅግ ወሳኝ መሣሪያ እና እንዲሁም ለኮሌጅ እና ለሙያ ስኬታማነት በተሻለ መንገድ የሚያዘጋጅ ነው። ውጤ ቶቹም ልጅዎ ምን እየተማረ እንደሆነ በተሻለ ሁኔታ ግንዛቤ እንዲያገኙ እና ለማሻሻልም የት የት እካባቢስ እርዳታ እንደም ናደርግላቸው ለማወቅ ይረዳል።

ተማሪ ልጅዎ፣ ለዚህ ለአዲስ ተፈታታኝ ሁኔታ ታጥቀው ሲነሡ፣ እነሱን ለመርዳት ከእኛ ጋር እንዲሰለፉ እጠይቅዎታለሁ። ስለ PARCC ከዚህ ደብዳቤ ጋር የተካተቱ ብዙ መረጃዎች አሉ። እባክዎን የፈተና ቀናትን እና የትኞቹ ክፍሎች እና የትምህ ርት ዐይነቶች ለፈተና እንደሚቀርቡ ለማጣራት እርግጠኛ ይሁኑ። ጥያቄዎች ካሉዎት የልጅዎን ትምህርት ቤት ርእሠ መም ህር ያነጋግሩ። ወይንም dcps.testing@dc.gov.ን ይጎብኙ።

እኛ ዲሲፒኤሶች ነን፣ እና ይህንንም ተግባራዊ እናደርጋለን!

ከልባዊ ሠላምታ ጋር፣

Kaya Henderson
ቻንስለር

1200 First Street, NE | Washington, DC 20002 | T 202.442.5885 | F 202.442.5026 | dcps.dc.gov